# የተበላሸ ማሞቂያ ወይም የማቀዝቀዣ መገልገያ መተካት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሐብት ይወቁ።

ነዋሪዎች የተበላሸ ማእከላዊ የአየር ኮንዲሽኒንጋቸውን፣የሙቀት ሲስተሞቻቸውን፣ ሙቅ የውሃ መያዣዎቻቸውን እንዲሁም የበለጠ ውጤታማ ሲስተም ጋር ያሉ የጭስ ማውጫ መሰንጠቂያዎቻቸው እንዲተካላቸው ማመልከት ይችላሉ። እኛ —የዲሲ መንግስት— በአካባቢ ካለ ትርፋማ ካልሆነ ድርጅት ጋር ለአዲሱ ሲስተም አብረን በመስራት ጠጋኝ ባለሙያ ሲስተሙን እንዲገጥም ቀጥረናል።

ይህ ፕሮግራም የድንገተኛ ሜካኒካል ሲስተሞች ፕሮግራም በመባል ሲታወቅ በሃይልና አካባቢ ክፍል ይቀርባል።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ መግለጫዎችበሙሉ እውነት ከሆኑ፣ ብቁ ነዎት ማለት ነው፡

● የሚኖሩት በተከራዩት ወይም የራስዎ በሆነ የአንድ ቤተሰብ ቤት ውስጥ ከሆነ (ወይም አራት ወይም አምስት ክፍሎች ያሉት ህንጻ)።

● ቤትዎ ዲሲ ውስጥ ከሆነ።

● ቤትዎ በሐራጅ ሊሸጥ ካልሆነ።

እንዲሁም ከእነዚህ መግለጫዎች ውስጥአንዱ ትክክል ነዉ፡

● ቤተሰብዎ ከሚከተሉት ፕሮግራሞች ቢያንስ በአንዱ ድጋፍ የሚያገኝ ከሆነ፡ Temporary Assistance for Needy Families (TANF፣ ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚሰጥ ጊዜያዊ እርዳታ) ወይም Supplemental Security Income (SSI፣ ተጨማሪ የዋስትና ገቢ) ወይም

● የቤተሰብዎ አመታዊ አጠቃላይ ገቢ — ግብር ከመክፈልዎ በፊት ያለው የእርስዎ ገቢ— በቤተሰብዎ መጠን ላይ ተመስርቶ ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች ነው። ገቢዎን ለማስላት፣ ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ አዋቂ ሰዎች ስራ በመስራት ገቢ የሚያገኙትን ገንዘብ ይደምሩ። ከዚያ፣ ከ 18 አመት በታች ያሉትን ልጆች አጠቃልሎ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው ከማህበራዊ ዋስትና፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም የጡረታ ክፍያዎች የሚያገኘውን ገንዘብ ይደምሩ። ለማረጋገጥ ከስር ያለውን ሰንጠረዥ ይጠቀሙ።

| የቤተሰብ መጠን (ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ |
|---|---|
| 1 | $32,814 |
| 2 | $42,911 |
| 3 | $53,007 |
| 4 | $63,104 |
| 5 | $73,201 |
| 6 | $83,297 |
| 7 | $85,190 |
| 8 | $87,804 |

# ያመልክቱ።

1. ፍጆታዎችዎን እንዲከፍሉ ለሚረዳዎት የLow Income Home Energy Assistance Program (LIHEAP፣) በማመልከት ይጀምሩ። በዚህ ፕሮግራም መጀመሪያ ላይ በማመልከትዎ፣ እኛ —የዲሲ መንግስት— ለአስቸኳይ የሚካኒካዊ ሲስተሞች መተካት ገቢዎ ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች መሆኑን ያረጋግጣል። ቀድመው LIHEAP ከተቀበሉ፣ ማመልከቻውን ለአስቸኳይ ምትክ ለማግኘት በ(202) 299-3316 ላይ ይደውሉ እና ወደ 2ተኛ እርምጃ ይቀጥሉ።

○ ***ለእርስዎና በቤተሰብዎ*** እያንዳንዱ ሰው የሚከተሉትን መረጃዎች ይሰብስቡ። ቢያንስ በአንዱ ዶክመንቶችዎ የእርስዎን ሙሉ ስም መዘርዘር አለበት እንዲሁም እርስዎ በዲሲ ውስጥ እንደሚኖሩ ለማሳየት የዲሲ አድራሻ መኖር አለበት። እንዴት እንደሚያመለክቱ ባለው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ፣ሰነዶችዎን ቅጂ ማድረግ ወይም ስካን ማድረግ ሊያስፈልግዎ ይችላል።

■ ፎቶ ያለባቸው መታወቂያዎች (ልክ እንደ መንጃ ፈቃድ ያሉ)

■ የማህበራዊ ዋስትና ካርዶች ወይም የውጭ ዜጋ ምዝገባ ቁጥሮች

■ በጣም የቅርብ የኤሌክትሪክ፣ ጋዝ፣ ዘይት እንዲሁም/ወይም የውሃ ክፍያዎች

■ የቅርብ የክፍያ ደረሰኞች፣ የማህበራዊ ዋስትናመግለጫዎች፣ የጡረታ መግለጫዎች፣ የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅም መግለጫዎች፣ የልጅ ድጋፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም የታክስ ተመላሾች (ለእርስዎ የሚሆን ሁኔታ ጋር የሚተገበሩ ሰነዶች ብቻ ያስፈልጉዎታል)

○ በኦንላይን ወይም በፓስታ መልእክት ለማመልከት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ይምረጡ፡

■ የኦንላይን LIHEAP ማመልከቻን ይሙሉ። ለመጀመር በመለያ መግቢያ እንዲፈጥሩ ይጠየቃሉ። ለአየር ንብረት ለውጥ እርዳታ ፍላጎት እንዳለዎት ይምረጡ። የሰነዶችዎን ፎቶዎች ወይም ስካኖች ወደ ማመልከቻው እንዲሰቅሉ ያስፈልጋል።

■ በፖስታ መልእክት ለማመልከት የተሞላውን የ LIHEAP የወረቀት ማመልከቻ እና የሰነዶችዎን ቅጂዎች ፕሪንት አድርገው ወደ The Department of Energy & Environment; 1200 First Street NE, 5th Floor; Washington, DC 20002 ላይ ይላኩ። ማመልከቻውን ፕሪንት ማድረግ የማይችሉ ከሆነ፣ በማንኛውም ሰዓት በ 311 ላይ በመደወል ማመልከቻዎን እንድንልክልዎት ሊጠይቁን ይችላሉ። ሰነዶችዎን ኮፒ ማድረግ ይኖርብዎታል። እባክዎ ኦሪጂናል ሰነዶች አይላኩ።

○ የተሟላ የ LIHEAP ማመልከቻዎን በተቀበልን በ 2 የስራ ቀና ውስጥ ለ LIHEAP ተቀባይነት ካገኙ፣ በኢሜይል እናሳውቅዎታለን። ለ LIHEAP ተቀባይነት ካገኙ፣ ለአስቸኳይ የሚካኒካዊ ሲስተሞች ምትክ ለማመልከት ወደ 2ኛ እርምጃ ይሂዱ።

2. መገልገያው እንደተበላሸና ለማስጠገን ምን ያህል ወጪ እንደሚያስወጣ ለማሳየት የሚያስችሉ ሰነዶችን ይሰብስቡ። ከ Washington Gas ቀይ መለያ ወይም ጥገና የሚያደርገው ድርጅት በራሱ ባለአርማ ወረቀት ላይ የጻፈው ግምት ሊሆን ይችላል።

3. ለአስቸኳይ የሚካኒካዊ ሲስተሞች ምትክ ያለውን ማመልከቻ ይሙሉ። ፍላጎት ካለዎት የቤትዎን ሙቀት እና የኤሌክትሪክ አጠቃቀም በተመሳሳይ ጊዜ ለመቀነስ ለእርዳታ ማመልከት ይችላሉ።

4. ቤትዎን ከተከራዩ፣ አንዳንድ ተጨማሪ የማመልከቻ ጥያቄዎችን ለማሙላት ከእርስዎ አከራይ ጋር ክትትል እናደርጋለን። በገቢያቸው ላይ ተመርኩዞ፣ የመተኪያውን አንዳንድ ክፍል እንዲከፍሉ አከራይዎን ልንጠይቅ እንችላለን።

በማንኛውም ጊዜ ላይ ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

**ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?**

1. እኛ —የዲሲ መንግስት— የእርስዎን የድንገተኛ ጊዜ የሜካኒካል ሲስተሞች ፕሮግራም ማመልከቻዎን እንገመግማለን።
2. በአንድ የስራ ቀን፣ በሂደቱ ውስጥ እንዲረዳዎ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ለትርፍ የማይሰራ ድርጅት ጋር እናገናኝዎታለን።
3. ለትርፍ የማይሰራው ድርጅት ወደቤትዎ ለመምጣት እንዲጎበኙ ቀጠሮ በማስያዝ የተበላሸ መገልገያ መሳሪያ ወይም ሲስተም መኖሩን ያጣራል።
4. ለትርፍ የማይሰራው ድርጅት ምትኮቹን በሶስት ቀናት ውስጥ ገዝቶ የሚገጥም አብሮዎት የሚሰራ የጥገና ባለሙያ ጋር ያገናኝዎታል።

5. በገጠማ ወቅትና ከገጠማ በኋላ በትክክል መገጠሙን ለማረጋገጥ የምትክ ሲስተሙን እንመረምራለን።

ለዚህ ፕሮግራም ተቀባይነት ካላገኙ፣ እርስዎን ለማሳወቅ እንደውልልዎታለን እንዲሁም ኢሜይል እናደርግልዎታለን።

**ሁሉም ብቁ አመልካቾች የተበላሹ የመገልገያ መሳሪያዎቻቸው ይተካላቸዋል?**
አይ፣ የገንዘብ ድጋፍ ለአስቸኳይ ምትኮች የሚደረገው መጀመሪያ በመጣ፣ መጀመሪያ በተስተናገደው መሰረት ላይ ነው። ብዙውን ጊዜ፣ ለሁሉም ብቁ አመልካቾች በቂ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ አለን።

**ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?**
ለፍጆታዎችዎ እንዲከፍሉና የአስቸኳይ ሜካኒካል ሲስተሞች ምትክ እንዲያገኙ ለሚረዳዎ ለእኛ ዝቅተኛ ገቢ የቤት ሃይል እርዳታ ፕሮግራም ማመልከት አለብዎት። ለዚህ ፕሮግራም ማመልከት እኛን —የዲሲ መንግስትን— ገቢዎን ለማረጋገጥ ይረዳናል።

**ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?**
መጀመሪያ በገጹ የታችኛው ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ። አሁንም ድረስ ጥያቄዎች ካለዎት፣ የእኛን የተመጣጣኝነትና ውጤታማነት ቡድንን ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm በ (202) 299-3316 (202) ላይ ደውለው ያግኙን። ወይም በ doee@dc.gov ላይ በርዕሰ መስመር “Emergency Mechanical System Replacement Question” በሚል ኢሜይል ሊያደርጉልን ይችላሉ።

**በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**
በእኛ የፍጆታ ሀብቶች ገጽ ላይ ስለሌሎች እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ።

**ሌሎች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**
የተበላሸ መገልገያ መሳሪያ እንዳለኝ ለማሳወቅ ምን አይነት ሰነድ ማሳየት አለብኝ?
ከWashington Gas ቀይ መለያ ወይም ጥገና የሚያደርገው ድርጅት በራሱ ባለአርማ ወረቀት ላይ የጻፈው ግምት ሊሆን ይችላል። ካልተስተካከለ ወይም ካልተተካ መሥራት አደገኛ በመሆኑ ምክንያት የእሳት ማቀጣጠያው ከተዘጋ፣ ብዙውን ጊዜ በእሳት ማቀጣጠያው ላይ ለተጫነው መለያ፣ ቀይ መለያ መስጠት ይባላል፡፡ መለያው ቀይ ወይም የተለየ ቀለም ሊሆን ይችላል።

**አስቸኳይ የሜካኒካል ምትክ ከዚህ በፊት ከተቀበልኩ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?**
አዎ፣ ከዚህ በፊት ምትክ ከተቀበሉና አሁን ያ መሣሪያ ወይም የተለየ ማዕከላዊ የአየር ኮንዲሽኒንግ ሲስተም፣ የማሞቂያ ሲስተም፣ የሞቀ ውሃ ማጠራቀሚያ ወይም የጭስ ማውጫ መስመር መተካት የሚያስፈልገው ከሆነ፣ እንደገና ማመልከት ይችላሉ፡፡

**ማመልከቻዬ ተቀባይነትን ካላገኘ፣ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?**
የቤተሰብዎ ገቢ ከፕሮግራም ገደቡ በላይ ሆኖ ተቀባይነት ካላገኘ፣ የእርስዎ ወይም የቤተሰብዎ መጠን ሲለወጥ እንደገና ማመልከት ይችላሉ።

**በ SNAP (በቀድሞው food stamps ተብሎ የሚጠራው) በኩል የምግብ እርዳታ አገኝቻለሁ። ያ እኔን ለዚህ ፕሮግራም ብቁ ያደርገኛል?**
የምግብ ድጋፍ በተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም (SNAP) በኩል ካገኙ፣ ለዚህ ፕሮግራም ብቁ እንደሆኑ ለማየት የቤተሰብዎ ገቢ ከፕሮግራም ገደቦቹ በታች መሆናቸውን ማጣራት ይኖርብዎታል። ለዚህ ፕሮግራም ብቁ መሆንዎትን ለማረጋገጥ SNAP መቀበል ብቻውን በራሱ በቂ አይደለም። ይሁን እንጂ፣ SNAP ከተቀበሉ በዝቅተኛ ገቢ የቤት ሃይል እርዳታ ፕሮግራም (LIHEAP) በኩል ፍጆታዎችዎን ለመክፈል የሚሆን እርዳታ ላይ ብቁ ኖት።

**ቤተሰቤ ምንም አይነት ገቢ የለውም። ያንን እንዴት ላስረዳ እችላለሁ?**
ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ የሌለው ከሆነ፣ ከማመልከቻዎ ጋር ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ሰነድ ማስገባት ይችላሉ፡

- በውል አዋዋይ ባለስልጣን የተረጋገጠ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣
- በ Department of Employment Services ((DOES፣ ቅጥር አገልግሎቶች ክፍል) ድረ ገጽ “ቀሪ ሂሳብ”ዎ ዜሮ እንደሆነ የሚያሳይ የእርስዎ “ይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ መገለጫ” ቅጽበታዊ ገጽ እይታ፣ (ምሳሌውን ይመልከቱ)፣
- ከቀድሞ አሠሪዎ ከአሁን በኋላ ወደዚያ እንደማይሠሩ የሚገልጽ ደብዳቤ (ከስራ ከለቀቁ ግን እስካሁን ድረስ የሥራ አጥነት ጥቅሞችን በ DOES እያገኙ ካልሆነ)፣ ወይም
- ከ District of Columbia Housing Authority (DCHA፣ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመኖሪያ ቤት ባለስልጣን) የመጣው ደብዳቤ የሚገልጸው ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ እንደሌለው ነው።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*